# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

## የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝ እና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ

### የኢንተርፕራይዝ ወይም ኢንዱስትሪ ገበያ ልማትና ፕሮሞሽን

### ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 116/2014

2014 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>

## መግቢያ

መንግስት የጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ዘርፍ ፖሊሲና ስትራቴጂ በመቀረጽ ለስራ ፈላጊ ዜጎች የስራ ዕድልን በመፍጠርና በከተማችን የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም የወጣቶችና ሴቶች ተጠቃሚነትን ለማሳደግ ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል፡፡ በዚህ መሰረት በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት የተደራጁ ዜጎችን የገበያ ድጋፍ በመስጠት በተለይም በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ተደራጅተው የሚሰሩ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የውጭ ምርት እንዲተኩና በገበያው ላይ የሚታየውን የአቅርቦት ችግር በመቅረፍ ለከተማዋ ነዋሪ ህብረተሰብ በተመጣጣኝ ዋጋ ምርትና አገልግሎት እንዲያቀርቡ እገዛ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ በመታመኑ፤

በተለያዩ የስራ ዘርፍ ተደራጅተው ወደ ሥራ የሚገቡ ነዋሪዎች በአካባቢ፣በክልልና በውጭ ገበያ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን የድጋፍ ሥርዓት በመዘርጋት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ላይ የሚገኝ ቢሆንም እስካሁን ያለው የገበያ ድጋፍ አሰጣጥ ሁኔታ የኢንተርፕራይዞችን ብቃትና ተወዳዳሪነት የማያበረታታና ውስን ኢንተርፕራይዞችን ብቻ የሚያሳትፍ የነበረ በመሆኑ፤

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን አገልግሎቶች ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ከሚፈልጉት ድጋፍ አንፃር ፍትሃዊነት የጎደለው፤ ግልጽነትና ተጠያቂነት የሌለው፤ የኢንተርፕራይዞችን ወይም ኢንዱስትሪዎችን ምልልስ የሚጨምር፤ ለብልሹ አሰራር ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ከመፍጠር አንፃር ክፍተት የነበረበት በመሆኑ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታትና ወጥነት ያለው አሰራር ለመዘርጋት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝ እና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 ዓ.ም አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ (2) ተራ ፊደል (ሠ) መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የኢንተርፕራይዝ ወይም ኢንዱስትሪ ገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 116/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
2. **"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስራ፤ኢንተርፕራይዝ እና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ነው፤
3. **"ጽህፈት ቤት"** ማለት በክፍለ ከተማ ወይም በወረዳ የሚገኝ የስራ፤ ኢንተርፕራይዝ እና ኢንዱስትሪ ልማት ጽህፈት ቤት ነው፤
4. **"ኢንተርፕራይዝ"** ማለት በንግድ ህጉ መሰረት ህጋዊ ሰዉነት ያገኘ ኢንተርፕራይዝ ነው፤
5. **"ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ"** ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት ፤የቤተሰብ አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞች ጨምሮ እስከ 5 ሰዎች ቀጥሮ የሚያሰማራና የጠቅላላ ካፒታል መጠን ህንፃን ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ እስከ ብር 50,000.00/ሃምሳ ሺ/ ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ እስከ ብር 100,000.00/አንድ መቶ ሺ/ድረስ የሆነ ኢንተርፕራይዝ ነው፤
6. **"አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ"** ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት ፤ የቤተሰብ አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ ከ6 እስከ 30 ሰዎች የሚያሰማራና የጠቅላላ ካፒታል መጠን ህንፃን ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,001.00/ ሃምሳ ሺ አንድ/እስከ ብር 500,000.00/አምስት መቶ ሺ/ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር 100,001.00/አንድ መቶ ሺህ አንድ/ እስከ ብር 1,500,000.00/ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ/ ድረስ ያለ ኢንተርፕራይዝ ነው::

7. **“መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ”** ማለት አንድ ኢንተርፕራይዝ የኢንዱስትሪውን ባለቤት፣ የቤተሰቡን አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ ከ31 እስከ 100 ሰዎች ቀጥሮ የሚያሰራና የጠቅላላ ካፒታል መጠኑ ህንጻን ሳይጨምር በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ከብር 1,500,001(አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ አንድ) እስከ ብር 20,000,000 (ሃያ ሚሊዮን) የሆነ ኢንተርፕራይዝ ነዉ፡፡

8. **“ከፍተኛ ኢንዱስትሪ”** የኢንተርፕራይዙን ባለቤት፤ የቤተሠብ አባላትና ተቀጣሪ ሠራተኞች ጨምሮ ከ101 ሰው በላይ ቀጥሮ የሚያሠማራና የጠቅላላ ሀብት መጠን በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር 20,000,00 በላይ የሆነ አምራች ኢንዱስትሪ ነዉ፡፡

9. **“የገበያ ጥናት”** ማለት፡- በማያቋርጥ ሁኔታ ከገበያ ላይ መረጃ መሰብሰብ፡ መተንተንና ለውሳኔ እንዲመች አድርጎ የመቀየር ሂደት ማለት ነው፡፡

10. **“ገበያ”** ማለት በአካባቢ፣ በክልልና በውጪ ሀገር ደረጃ የሚገኝና የጥቃቅን፤ አነስተኛ፤መካከለኛና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ምርትና አገልግሎት በዋጋ ተወዳዳሪ ሆነው የሚቀርቡበት ስፍራ ነው፤

11. **“ግብይት”** ማለት በሻጭ እና በገዥ መካካል የሚካሄድ የምርትና አገልግሎት ልውውጥ ማለት ነው፤

12. **“የገበያ ትስስር” ማለት** በሀገር አቀፍ እና በውጪ ሀገር በሚፈጠሩ የገበያ ዕድሎች በነጻ ገበያ መርህ ላይ በተመሰረተ የገበያ ውድድር የእርስ በርስ፤ ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች በንዑስ ተቋራጭነት፤ በአውትሶርሲንግ፤ በፍራንቻይዚንግ በአውትግሮወር እና በሌሎችም የግብይት ዘዴዎች ተሳስረው ምርትና አገልግለት በማቅረብና በመቀበል የሚደረግ የገበያ ልውውጥ ነው፤

13. **“የሀገር አቀፍ ገበያ”** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ እና ከአዲስ አበባ ክልል ውጪ በየትኛውም የሀገሪቱ ክልል ከሚገኝ ማንኛውም የመንግስት ድርጅት፣መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት፣ የህብረት ሥራ ዩኒዮን በከተማችን ካሉ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ጋር በገበያ ማስተሳሰር ነው፤

14. **“የውጪ ገበያ”** ማለት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚካሄድ የንግድ ወይም የግብይት ሥርዓት ሆኖ በሀገር ውስጥ የሚገኙ ኢንተርፕራይዞችወይም ኢንዱስትሪዎች በውጭ

ሀገር ከሚገኙ ተቋማት ጋር ምርትና አገልግሎታቸውን በተለያዩ የግብይት መንገዶች የሚለዋወጡበት ሥርዓት ነው፤

15. **"እሴት መጨመር"** ማለት አንድ ምርት ወይም አገልግሎት በፊት ከነበረበት አካላዊ ወይም ውስጣዊ ይዘት ላይ በመጨመር ወይም በመቀነስ ተጨማሪ ገጽታ መፍጠር ነው፤

16. **"ንዑስ ስራ ተቋራጭነት"** ማለት የመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ወይም የመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በመለየት ሥራውን በከፊል በኢንተርፕራይዞች ወይም በኢንዱስትሪዎች እንዲሰራ ውል በመፈጸም የሚካሄድ የግብይት ሥርዓት ነው፤

17. **"አውትሶርሲንግ"** ማለት በመንግስታዊ፤ መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት እና ኩባንያዎች የሚከናወኑ ተግባራትን በመለየት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ምርቱ ወይም አገልግሎቱ በጥቃቅን፤ አነስተኛ፤ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የሚቀርብበት የግብይት ሥርዓት ነው፤

18. **"ፍራንቻይዚንግ"** ማለት በተወሰኑ ለየት ባሉ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ከአምራቹ ወይም አገልግሎት ሰጪው ወይም አከፋፋዩ ድርጅት ጋር የንግድ ስምምነት ውል በመፈጸም በውሉ መሰረት በውል ሰጪው የንግድ ስም፤ምልክትና ፈቃድ ለመስራት የሚያስችል የንግድ አሰራር ሥርዓት ነው፤

19. **"አውትግሮወር"** ማለት በአግሮፕሮሰሲንግ ሥራ ላይ የተሰማሩ ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጓቸውን የግብርና ግብዓቶች በኢንተርፕራይዞች ተመርቶ ወይም እሴት ተጨምሮበት ከኢንዱስትሪዎች ጋር በሚደረግ ስምምነት ውል በመፈጸም የሚቀርብበት የንግድ አሰራር ሥርዓት ነው፤

20. **"የገበያ ዳይሬክተሪ"** ማለት የኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች አድራሻ መረጃ የምናስተዋውቅበት የማስተዋወቂያ ዘዴ ነው፤

21. **"ኢ-ኮሜርስ"** ማለት ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች በተለያዩ ድረ ገጾችን በመክፈት ምርትና አገልግሎታቸውን የሚያስተዋውቁበትና የሚሸጡበት የግብይት መሳሪያ ነው፤

22. **“ካታሎግ”** ማለት ኢንርተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ምርትና አገልግሎታቸውን በዝርዝር በህትመት በፎቶግራፍ በማስደገፍ ምርትና የምርት ናሙናቸውን የሚያስተዋውቁበት መሳሪያ ነው፤

23. **“ቴሌማርኬቲንግ”** ማለት በስልክ ደንበኞችን በመለየት የምርት ናሙና የሚያስተዋውቁበት እና ሽያጭ የሚካሄድበት የግብይት መንገድ ነው፤

24. **“የኢንተርፕራይዝ ደረጃ ሽግግር”** ማለት አንድ ኢንተርፕራይዝ ወይም ኢንዱስትሪ በዕድገት ደረጃው የሚሰጠውን ድጋፍ ተጠቅሞ በገበያ ላይ በዋጋ፣ በጥራትና በአቅርቦት ተወዳዳሪ ሆኖ ወደ ቀጣይ የዕድገት ደረጃ የሽግግር መስፈርቶቹን በማሟላት መሻገር ሲችል ነው፤

25. **“የምሥረታ ወይም ጀማሪ ደረጃ”** ማለት ኢንተርፕራይዞችን ለመመሥረት ፍላጎት ያላቸው ነዋሪዎች በግል፣ በህብረት ሽርክና ማህበር፣ ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና አክሲዮን ማህበር ተደራጅተው ህጋዊ ሰውነት በማግኘት ማምረትና አገልግሎት መስጠት ተግባር የሚጀምሩበት ነው፤

26. **“የታዳጊ ወይም መስፋፋት ደረጃ”** ማለት አንድ ኢንተርፕራይዝ የሚሰጠውን ድጋፍ ተጠቅሞ በገበያ ላይ በዋጋ፣ በጥራትና በአቅርቦት ተወዳዳሪ ሲሆንና ትርፋማነቱ ቀጣይነት ሲኖረው ነው:: በዚህ ደረጃ ያለ ኢንተርፕራይዝ በምሥረታ ደረጃ ከነበረው ቀጥሮ የሚያሠራው የሰው ኃይል ቁጥርና የጠቅላላ ሃብት መጠን ዕድገት በተጨማሪም ኢንተርፕራይዙ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት የሚጠቀም ነው፤

27. **“የመብቃት ደረጃ”** ማለት አንድ ኢንተርፕራይዝ የሚሰጠውን ድጋፍ ተጠቅሞ በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪና ትርፋማ ሆኖ የገበያ ድርሻውን ለማሳደግ ተጨማሪ ኢንቨስትመንት በሥራ ላይ ካዋለና ለዘርፉ የተቀመጠውን ትርጓሜ መስፈርት ሲያሟላና ወደ ታዳጊ መካከለኛ ሲሸጋገር ወይም በአለበት ደረጃ ጥቃቅን ወይም አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ በመሆን በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪና ትርፋማ ሆኖ የሚቀጥል ሲሆን ነው፤

28. **“ታዳጊ መካከለኛ ደረጃ”** ማለት ለአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የተቀመጠውን የሰው ሃይልና ጠቅላላ ሃብት መጠን የመብቃት የዕድገት ደረጃ በማለፍ ወደ ኩባንያ ደረጃ የተሸጋገረ የኢንተርፕራይዝ የዕድገት ደረጃ ነው፤

29. **"ክላስተር"** ማለት በአንድ አካባቢ ተሰብስበው ብዛት ያላቸውና ተመጋጋቢ የሆኑ ምርቶችንና አገልግሎቶችን የሚያቀርቡና ተመሳሳይ ኃላፊነትንና መልካም አጋጣሚውንም የሚጋሩ ተቋማት ስብስብ ነው፤

30. **"የተጣራ ካፒታል"** ማለት አንድ ኢንተርፕራይዝ ጠቅላላ የሃብት መጠን ሲቀነስ እዳ ነው፤

31. **"ፕሮሞሽን" (የምርት ወይም የአገልግሎት ማስታወቂያዎች)** ማለት ምርትን ወይም አገልግሎትን ለማስተዋወቅ የህትመትና ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች፤ንግድ ትርዒትና ባዛር፣ ብሮሸር፣ በራሪ ወረቀት፣ ዳይሬክተሪ፣ ካታሎግ፣ ድረ ገጽ፣ ቢዝነስ ካርድ፣ ቋሚ የማስታወቂያ ሰሌዳና የምርት ማሸጊያን ያካተተ ነው፤

32. **"የታከለ ዋጋ"** ማለት ከጠቅላላ ወጪ ላይ ከውጪ ሀገር ለሚመጡ ጥሬ ዕቃዎች እና ሌሎች አቅርቦቶች እንዲሁም ከውጪ ሀገር ለተገኘ አገልግሎት የተደረገ ወጪ ተቀንሶ የሚቀረው ወጪ ነው፤

33. **"ጥሬ ዕቃ"** ማለት አንድን ምርት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት የምንጠቀምበት ግብዓት ነው፤

34. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

3. **<u>የጾታ አገላለፅ</u>**

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

4. **<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ መመሪያ በቢሮው፣ በጽህፈት ቤቶች እና በኢንተርፕራይዞች ወይም በኢንዱስትሪዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

5. **<u>የመመሪያው ዓላማ</u>**

ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የሚያመርቱትን ምርትና የሚሰጡትን አገልግሎት በጥራት፣ ዋጋና በብዛት በማቅረብ ተወዳዳሪ እንዲሆኑና የአገር እና አለም አቀፍ የገበያ ዕድሎችን አሟጦ መጠቀም የሚያስችል ግልጽና ተጠያቂነት ያለው አሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ብቁና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማስቻል ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## የገበያ ትስስር ዓይነቶች እና የግብይት ሥርዓቶች

### 6. የገበያ ትስስር ዓይነቶች

1. በአካባቢ የሚፈጠር የገበያ ትስስር፤
2. በክልል የሚፈጠር የገበያ ትስስር፤
3. በውጪ ሀገር የሚፈጠር የገበያ ትስስር፡፡

### 7. ለኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች በአካባቢ ስለሚፈጠር የገበያ ትስስር ዓይነቶች

በአካባቢ የሚፈጠሩ የገበያ ትስስር ዓይነቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

1. መንግስታዊ ከሆኑ ተቋማት ጋር የሚፈጠር የገበያ ትስስር፤
2. መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር የሚፈጠር የገበያ ትስስር፤
3. በኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች መከካል እርስ በርስ የሚፈጠር የገበያ ትስስር፤
4. በሌሎች የገበያ አማራጮች በቅዳሜ እና እሁድ፤ በንግድ ትርኢትና ባዛር፤ በምርት ማሳያና መሸጫ ምርቶችን በማስገባት የሚፈጠር የገበያ ትስስር፤ ይሆናሉ፡፡

### 8. ኢንተርፕራይዞች የአካባቢ ገበያዎችን አሟጦ ስለመጠቀም

1. ኢንተርፕራይዞች መንግስታዊ ከሆኑ ተቋማት የሚፈጠር የገበያ ትስስር፤ በአስተዳደሩ የግዢ መመሪያ መሰረት ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት፣ ለተደራጁ ኢንተርፕራይዞች ልዩ አስተያየት በዋጋ ላይ በሚደረግ ውድድር ወቅት በሚከተለው መሠረት ተፈፃሚ መደረግ አለበት፡-

   ሀ) ለመድሀኒት እና የህክምና መሳሪያዎች ግዢ 25% /ሃያ አምስት በመቶ/ ቅናሽ የሚያገኙ መሆን አለበት፤

   ለ) ለሌሎች ዕቃዎች ግዢ 15% /አስራ አምስት በመቶ/ ቅናሽ የሚያገኙ መሆን አለበት፤

ሐ) ለግንባታ ሥራና የምክር አገልግሎት ግዥዎች 7.5% / ሰባት ነጥብ አምስት በመቶ/ ቅናሽ የሚያገኙ መሆን አለበት፣

2. የሚደረገው ልዩ አስተያየት መድሐኒቱን ወይም የህክምና መሳሪያውን ወይም ዕቃውን ለማምረት ከወጣው ጠቅላላ ዋጋ ወጪ 35% /ሰላሳ አምስት በመቶ/ እና ከዚያ በላይ በኢትዮጵያ ውስጥ የታከለ እሴት መሆኑን የሚያስረዳ በተመሰከረለት ኦዲተር የተረጋገጠ ማስረጃ ሲቀርብ ቅናሽ መደረግ አለበት፤

3. ማንኛውም የግንባታ ዘርፍ ወይም የምክር አገልግሎት ሥራ የተፈቀደው ልዩ አስተያየት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች በሙሉ ሲያሟላ መሆን አለበት፡-

   ሀ) ማህበሩ በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት የተቋቋመና እና ዋና መስሪያ ቤቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን፣

   ለ) ማህበሩ አክሲዮን ወይም የካፒታል ድርሻ ከ50%(ሃምሳ በመቶ) በላይ በኢትዮጵያውያን የተገዛ ከሆነ፣

   ሐ) ከማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መካከል ከ50%(ሃምሳ በመቶ)በላይ ኢትዮጵያውያን ከሆኑ፣

   መ) ማህበሩ ቁልፍ ሠራተኞች መካከል ቢያንስ ከ50% (ሃምሳ በመቶ) ኢትዮጵያውያን ከሆኑ፤

4. በቢሮው የተቋቋሙ ጥቃቅን፣ አነስተኛ ተቋማት፡-

   ሀ) ከአገር ውስጥ አቅራቢዎች ጋር በሚያደርጉት ውድድር 3% (ሦስት ከመቶ) ልዩ አስተያየት መደረግ አለበት፤

   ለ) ግዢው በአለም አቀፍ የግዥ ዘዴ የሚፈፀም ሲሆን የተፈቀደው ልዩ አስተያየት ብቻ ተፈፃሚ መደረግ አለበት፤

   ሐ) በጨረታ ማስከበሪያ፣ በውልማስከበሪያ እና የቅድመ ክፍያ ዋስትና ምትክ ተቋማቱ ካደራጃቸው አካል የሚሰጥ የዋስትና ደብዳቤ ተቀባይነት ያለው መሆን አለበት፤

መ) ለጨረታው የተዘጋጀውን የጨረታ ሠነድ በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋምነት የተቋቋሙበትን የህጋዊነት ማስረጃ በማሳየት ያለክፍያ በነፃ መሰጠት አለበት፡

9. <u>በመንግስት ተቋማት በሚፈጠሩ የገበያ ድጋፎች ኢንተርፕራይዝ ወይም ኢንዱስትሪ ምልመላ</u>

በመንግስት ተቋማት በሚፈጠሩ የገበያ ድጋፎች ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ምልመላ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1. የገበያ ዕድሉን የሚፈጥረው ተቋም በሚያወጣው መስፈርት መሰረት ማከናወን አለበት፤
2. ገበያውን የፈጠረው ተቋም የሚያወጣቸው መስፈርቶች ከኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የዕድገት ደረጃ ጋር የማይገናዘቡ ሆኖ ሲገኝ ገበያውን ከሚፈጥረው ተቋም ጋር በመወያየት በሚዘጋጁ መስፈርቶች መሰረት የሚፈጸም መሆን አለበት፤
3. የገበያ ዕድሉን የሚፈጥረው ተቋም መስፈርት ሳያዘጋጅ ስራውን ለተደራጁ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች መስጠት የፈለገ ከሆነ ያደራጃቸው አካል ስራው ከሚጠይቀው የሰው ኃይልና ካፒታል አንፃር መስፈርት በማዘጋጀት የሚፈጸም መሆን አለበት፤
4. ኢንተርፕራይዙን ወይም ኢንዱስትሪዎችን ያደራጀው አካል የመመልመያ መስፈርቱን ግልጽ በማድረግ በውድድር ላይ ተመስርቶ የሚፈጸም መሆን አለበት፤
5. የመመልመያ መስፈርቱ ለኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ግልጽ ሆኖ የሚቆይበት ጊዜ የገበያ ዕድሉን የሚፈጥረው ተቋም በሚያዘጋጀው መስፈርትና የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የሚፈፀም መሆን አለበት፡፡

10. <u>በየእድገት ደረጃው እና በየዘርፉ ሊፈጠር የሚችል የገበያ ትስስር መጠን በብር</u>

1. በየእድገት ደረጃው እና ዘርፉ ሊፈጠር የሚችል የገበያ ትስስር ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው አባሪ መሰረት ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) አንድ ገበያ ትስስር ከአንድ በላይ ለሆኑ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች እንደ ገበያው የብር መጠን በመስጠት የሚተገበር መሆን አለበት፤

ለ) ማንኛውም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ስራዎች ከጀማሪ ጥቃቅን እስከ መካከለኛ እስከሚደርስ ድረስ የሚፈጠርለት የገበያ ትስስር ተደምሮ ከብር 31,000,000.00 መብለጥ የለበትም፤

ሐ) ማንኛውም ኢንተርፕራይዝ በአገልግሎት ወይም ከተማ ግብርና ስራዎች ከጀማሪ እስከ መካከለኛ እስከሚደርስ ደረስ የሚፈጠርለት የገበያ ትስስሮች ተደምረው ከብር 13,000,000.00 መብለጥ የለበትም፤

መ) የአሰሪው መስሪያ ቤት የፈጠረውን የገበያ ትስስር ወቅታዊ መረጃ በመሰብሰብ መያዝ አለበት፤

ሠ) በመንግስት ፕሮጀክት ሆነ በመንግስት ግዢ ዕድል ያገኙ ኢንተርፕራይዞች ተገቢውን የእድገት ደረጃ እየተሰጣቸው የገበያ ትስስር ጣሪያ ሲደርሱ በገበያ ልማት እና በዕድገት ደረጃ ሽግግር ባለሙያ ክትትል እየተደረገ ወደ ቀጣዩ የዕድገት ደረጃ እንዲሸጋገሩ መደረግ አለበት፤

ረ) የገበያ ትስስር ድጋፍ ሲደረግ የኢንተርፕራይዙን አባላት ቁጥር ታሳቢ በማድረግ ቅድሚያ የሚሰጥ መሆን አለበት፤

ሰ) አንድ ጊዜ የገበያ ትስስር ያገኘ ኢንተርፕራይዝ ሁለተኛ ጊዜ ትስስር የሚደረግለት በዘርፉ መስፈርቱን የሚያሟሉ ሌሎች ኢንተርፕራይዞች የመጀመሪያ ትስስር ማግኘታቸውን በማረጋገጥ መሆን አለበት፤

ሸ) የገበያ ትስስር የሚደረግለት ኢንተርፕራይዝ የበጀት ዓመቱን የዕድገት ደረጃ ያሳደሰ መሆን አለበት፡፡

## 11. <u>ስለኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የገበያ ትስስር አሰራር</u>

1. የአከባቢ ተጨባጭ የገበያ ዕድሎችን በመለየትና በጥናት መሰራት አለበት፤
2. የገበያ ትስስር ሊፈጥሩ የሚችሉ አነስተኛ፤ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎችና ተቋማት በዝርዝር የመለየት ሥራ መሰራት አለበት፤
3. በየዘርፉ የተለዩ ኢንዱስትሪዎችና ተቋማት የምርት ወይም የአገልግሎት መጠን፤ ዓይነት፤ የጥራት ደረጃ፤ የማቅረቢያ ዋጋ የመለየት ሥራ መስራት አለበት፤
4. ኢንዱስትሪዎቹና ተቋማቱ ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚፈልጉትን ግብዓት፣ ምርት ወይም አገልግሎት በዝርዝር መለየት አለበት፤

5. የተለዩትን ዝርዝር መረጃዎች መሠረት በማድረግ እና የኢንተርፕራይዞችን ፕሮፋይል በማደራጀት በዕድገት ደረጃ መሰረት የመለየት፣ ግንዛቤ የመፍጠር እና የገበያ ትስስር ውል ገብተው እንዲሰሩ ማድረግ አለበት፤

6. ከከተማው የንግድና ዘርፍ ማህበራት ጋር የቅርብ ግንኙነትና የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም በስሩ ካሉት የንግድ ድርጅቶች፣ አማካሪዎችና ባለሙያዎች ጋር በመነጋገር በጥቃቅንና አነስተኛ እንዲሁም በመካከለኛና በከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች መካከል የሚፈጠረውን ትስስር የማሳደግ ስራ መሰራት አለበት፤

7. ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን ከሸማቾች መሰረታዊ ማህበራትና ዩኒየኖች ጋር የማስተሳር ስራ መሰራት አለበት፤

8. በየደረጃው ያሉ ኢንተርፕራይዞች ከኢንዱስትሪዎች ጋር ለማስተሳሰር የሚያስፈልጋቸው የክህሎት፣ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂ፣ የቦታና ሌሎች ድጋፎች የሚፈልጉ ሆኖ ሲገኝ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመሰራት ድጋፍ መደረግ አለበት፤

9. የኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን የዕርስ በርስ የገበያ ትስስር፣ ከአካባቢ ማህበረሰብ እና ከግለሰቦች ጋር የሚፈጠር የገበያ ትስስር ስራ ጥናት ላይ መሰረት በማድረግ መሰራት አለበት፤

10. በአካባቢ የሚገኙ የገበያ ዕድሎች አሟጦ ከመጠቀም አንፃር የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጥናት በመለየት ከሚመለከተው አካል ጋር በቅንጅት በመስራት የኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን ተጠቃሚነት የማሳደግ ስራ መሰራት አለበት፡፡

## 12.<u>የክልል ገበያን አሟጦ ስለ መጠቀም</u>

1. የክልል ተጨባጭ የገበያ ዕድሎችን በመለየትና በማጥናት መሰራት አለበት፤

2. በየክልሉ ከሚገኙ የግብርና ምርት አቅራቢ ዩኒየኖች፤ የህብረት ሥራ ማኅበራት እና ድርጅቶች በምርት ዓይነት፤ በአቅርቦት መጠን፤ በዋጋና በጥራት፤ በአዲስ አበባ ከተማ እና በክልሎቹ መካከል በሚኖር የትራንስፖርት ወይም የመጓጓዣ ወጪ ሁኔታ በዝርዝር መረጃ እንዲጠናቀር ማድረግ አለበት፤

3. ከአዲስ አበባ ከተማ ወደ ክልል ሊተሳሰሩ የሚችሉ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን በማጥናት ሊያቀርቡት የሚችሉትን ምርት በዋጋ፣ በጥራትና በመጠን በመለየት የማስተሳሰር ስራ መስራት አለበት፤

4. በክልሎች የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን ከአዲስ አበባ ከተማ ኢንተርፕራይዞች ጋር በየዘርፉ እንዲገናኙ ልምድ እንዲለዋወጡና የገበያ መረጃ እንዲያገኙ ማመቻቸት አለበት፤

5. በየክልሉ ያለውን እምቅ የገበያ ዕድል መረጃ በማሰባሰብ በየዘርፉ ያሉት ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው የግንዛቤ ስልጠና መሰጠት አለበት፤

6. በየክልሉ በሚዘጋጁ ኤግዚቢሽንና ባዛሮች ከአዘጋጁ ክልል ጋር በመነጋገር ኢንተርፕራይዞች እንዲሳተፉና በክልል ገበያ ውስጥ በመግባት ምርትና አገልግሎታቸውን እንዲያስተዋውቁ ማደረግ አለበት፤

7. የክልል የገበያ ዕድሎች አሟጦ ከመጠቀም አንፃር የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጥናት በመለየት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት የኢንተርፕራዞችን ተጠቃሚነት የማሳደግ ስራ መሰራት አለበት፡፡

13.<u>የውጪ ሀገር የገበያ ዕድሎችን አሟጦ ስለመጠቀም</u>

1. የውጪ ሀገር የገበያ ዕድሎችን በመለየትና በማጥናት መከናወን አለበት፤

2. ከኢትዮጵያ ውጪ ባሉ የአለማችን ክፍሎች የሀገራችን ምርቶች የሚገቡበትን ስልቶች በማጥናትና በመንደፍ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች መረጃውን እንዲያገኙ መደረግ አለበት፤

3. በውጭ ሀገር ተመርተው ወደ ሀገራችን የሚገቡና ለኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች በጥሬ ዕቃነት የሚያገለግሉ ምርቶችን በጥናት በመለየት በመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች በሀገር ውስጥ የሚመረቱበት መንገድ መመቻቸት አለበት፤

4. ወደ ኤክስፖርት ንግድ የመግባት አቅም ያላቸውን ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች በውጪ ሀገርም ርታቸውን ሊቀበሏቸው ከሚችሉ አካላት ጋር

ግንኙነት በመፍጠር ምርታቸውን እንዲያስተዋውቁ እና በውጭ ገበያ እንዲገቡ ድጋፍ መደረግ አለበት፤

5. በውጭ ሀገርና በሀገር ውስጥ በኢ-ኮሜርስ ምርትና አገልግሎታቸውን የማስተዋወቅ እና የመሸጥ አገልግሎት የሚሰጡ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በተለዩ መንገዶች ድጋፍ የሚሠጥበትን መንገድ መመቻቸት አለበት፤
6. በኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የሚመረቱና በውጭ ሀገራት ተፈላጊነት ያላቸውን ምርቶች በጥናት በመለየት ኤክስፖርት የማድረግ አቅም ያላቸው ኢንተርፕራይዞች መረጃ የመስጠት ስራ መሰራት አለበት፤
7. በውጭ ገበያ የመግባት አቅም ያላቸው ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የምርት ጥራትና ስታንዳርድ፤ የምርት ግብዓት መግለጫ፤ የአስተሻሸግ እና የክህሎት ስልጠና እንዲያገኙ መደረግ አለበት፤
8. በውጪ ሀገራት በሚዘጋጁ ኤግዚቢሽንና ባዛሮች ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ምርትና አገልግሎታቸውን እንዲያስተዋውቁ ድጋፍ መደረግ አለበት፤
9. ከንግድና ዘርፍ ማህበራት ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር በውጪ ሀገራት ከሚገኙ ካምፓኒዎችና ኢንቨስተሮች ጋር በከተማችን የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የጋራ የምክክር መድረክ በመፍጠር የገበያ ትስስር የሚያገኙበትን ሁኔታና ስልቶች በመንደፍ ተግባራዊ መደረግ አለበት፤
10. የውጪ ሀገር የገበያ ትስስርን በተመለከተ በጉዳዩ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን መሰራት አለበት፤
11. የውጪ ሀገር የገበያ ዕድሎችን ከመጠቀም አንፃር የሚያጋጥሙ ችግሮችን በጥናት በመለየት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት የኢንተርፕራይዞችን ወይም ኢንዱስትሪዎችን ተጠቃሚነት የማሳደግ ስራ መሰራት አለበት፡፡

## 14. <u>የግብይት ሥርዓት ዓይነቶች</u>

የገበያ ትስስር የሚፈጠርባቸው የግብይት ሥርዓት ዓይነቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

1. በንዑስ ተቋራጭነት ለሚሰማሩ ኢንተርፕራዞች የገበያ እድል መፍጠር አይነቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ) በማኑፋክቸሪንግና ኮንስትራክሽን ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን በእድገት ደረጃቸው በመለየት ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር በንዑስ ተቋራጭነት የግብይት ሥርዓት እንዲተሳሰሩ ማድረግ፡፡ ይህንንም ለማድረግ በከተማው የሚገኙ የግልና የመንግስት የልማት ድርጅቶችን የማነጋገር፤ የማሳመንና ያላቸውን የገበያ እድል መለየትና ለዚሁ ዕድል ዝግጁ የሆኑ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን ፕሮፋይል ማዘጋጀት፣ የምርትና አገልግሎት ጥራት ደረጃ መለየትና መረጃ ማደራጀት ያስፈልጋል፤

ለ) ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች እርስ በርስ የሥራ ዕድል በመፍጠር በንዑስ ተቋራጭነት ትስስር እንዲፈጠሩ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤

ሐ) አዳዲስ በሚጀመሩ የመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ውስጥ በንዑስ ተቋራጭነት የሚሰማሩበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት፤

2. በአውት ሶርሲንግ የግብይት ሥርዓት መፍጠር ጋር በተያያዘ፡-

ሀ) በመንግስት ተቋማት ውስጥ በሚሰጡ አገልግሎቶች ለኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች አውትሶርስ ሊደረጉ የሚገባቸውን ሥራዎች በማጥናት በየዘርፉ ትስስር መፍጠር፤

ለ) በመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር ትብብር መድረክ በማዘጋጀት በየኢንዱስትሪው አውትሶርስ ሊደረጉ የሚችሉ ምርቶችና አገልግሎቶችን በዝርዝር በመለየት ለጥቃቅንና አነስተኛ የሚሰጡበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት፤

ሐ) ለኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ስለ አውትሶርሲንግ የግብይት ስርዓቶች ግንዛቤ መፍጠር፤

3. በፍራንቻይዚንግ የግብይት ሥርዓት መፍጠር በተያያዘ፡-

ሀ) ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ከሀገር ውስጥ እና በውጪ ከሚገኙ ድርጅቶች ምርቶችን የንግድ ምልክታቸውን፤ የንግድ ፈቃዳቸውን፣ የምርት ስታንዳርዳቸውን በመጠቀም ምርቶችን እንዲያመርቱና አገልግሎቶችን እንዲያቀርቡ፤ እንዲያከፋፍሉ ወይም በኮሚሽን ለመሸጥ እንዲችሉ እንደየእድገት ደረጃቸው የገበያ ትስስር እንዲመቻች ይደረጋል፣

ለ) በፍራንቻይዚንግ የግብይት ሥርዓት የሚተሳሰሩ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች በሚቀበሉት የምርትና አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚጠበቅባቸውን የሙያና የሥራ ልምድን ጨምሮ ሌሎች በፍራንቻይዘሩ ድርጅት የሚቀመጡ መስፈርቶችን ማሟላት ይኖርባቸዋል፣

ሐ) የመካከለኛና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች የንግድ ምልክት፣ የንግድ ሥም፣ የንግድ ፈቃድና ሌሎች የቴክኖሎጂ ስልጠናዎችን ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በመስጠት በፍራንቻይዚንግ የግብይት ሰርዓት የሚሠጡ ከሆነ ልዩ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

## 15.<u>በፍራንቻይዚንግ የግብይት ሥርዓት ስምምነት ወቅት መከናወን የሚገባቸው ተግባራት</u>

1. የፍራንቻይዚንግ የንግድ ሥራ ፈቃድ ስምምነት ከመደረጉ በፊት በሚሰጠው የንግድ ስራ ያሉ የፈቃድ አሰጣጥ ሂደቶችና ዝርዝር ሁኔታዎች የሁለቱን ወገኖች ሙሉ መረጃ ፍላጎት ያካተተ መሆኑን አውቆ በጥንቃቄና በግልጽ መደራደር ይኖርባቸዋል፤
2. ሁለቱ ወገኖች በውል ተቀባይ ስለሚሰራው አገልግሎት በጋራ የገበያ እቅድ ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፤
3. የፍራንቻይዚንግ አገልግሎት በተመለከተ ሊኖሩ የሚችሉ ማንኛውም ክፍያዎችን በግልጽ በውል ስምምነቱ ላይ መካተታቸውንና ግልጽ ያልሆነ ክፍያ አለመኖሩን በጋራ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፤
4. የውል ተቀባይ የመነሻ ካፒታልና የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች በሙሉ በግልጽ መታወቅ ይኖርባቸዋል፤
5. ውል ተቀባይ አገልግሎቱ በሚሰጥበት አካባቢ ክልል ውስጥ ከውል ሰጪ ምርትና አገልግሎት ውጪ ወይም ከሌላ ተወዳዳሪ ድርጅት ውል ተቀብሎ መስራት አለመቻሉን በግልጽ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል፤
6. ውል ተቀባይ ፍራንቻይዝ ያደረገውን አገልግሎት የመስሪያ መሳሪያዎች ቀላል ጥገናዎች በውል ሰጪው በሚዘጋጅለት ማኑዋል መሠረት ጥገናውን በራሱ ማከናወን ይኖርበታል፡፡

## 16.<u>በአውትግሮወር የግብይት ሥርዓት መፍጠር</u>

1. የግብርና ውጤቶች የሆኑ በከፊል የማዘጋጀት፣ እሴት በመጨመር ለመካከለኛና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚያቀርቡ ኢንተርፕራይዞች በአውትግሮወር የግብይት ሥርዓት እንዲተሳሰሩ መደረግ አለበት፤
2. በየደረጃው የሚገኙ ጽህፈት ቤቶች በኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንተርፕራይዞች በአውትግሮወር የግብይት ሥርዓት ሊከናወኑ የሚችሉ ዝርዝር ሥራዎችን በመለየት ከመካከለኛና ከፍተኛ የአግሮፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች የማስተሳሰር ሥራዎች መከናወን አለበት፤
3. የክልል ኤጀንሲ ወይም ጽህፈት ቤት በአውትግሮወር የግብይት ሥርዓት የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን የአቅርቦት አቅም ለማሳደግ እንዲቻል በዩኒየን ወይም በሌላ ሕጋዊ አደረጃጀት ተደራጅተው እንዲሰሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለበት፤
4. በአወትግሮወር የግብይት ሥርዓት ምርቶቻቸውን ለመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ለሚያቀርቡ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ኢንዱስትሪዎቹ የሚፈልጉትን የምርት ዓይነትና ደረጃ እንዲያሟሉ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚሰጣቸው ሲሆን በተጨማሪም ከክልሉ የግብርና ቢሮ ወይም የግብርና ምርምር ተቋም ጋር በመቀናጀት ድጋፍ መደረግ አለበት፤፡፡
5. የግብርና ምርቶች በማቀነባበር (የአግሮፕሮሰሲንግ) ሥራ ላይ የተሰማሩ መካከለኛና ከፍተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጋቸውን በከፊል እሴት የተጨመረበት የግብርና ጥሬ እቃዎችን በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲቀርብላቸው የተቀናጀ ድጋፍ መደረግ አለበት፡፡

## 17.<u>የአውትግሮወር የግብይት ሥርዓት ስለማስፈፀም</u>

1. የመካከለኛና ከፍተኛ አግሮፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች የምርት እሴት ሰንሰለትን መሠረት በማድረግ በአውትግሮወር የግብይት ሥርዓት ውስጥ የእያንዳንዱ ተዋንያን ድርሻ በዝርዝር እንዲለይ በማድረግ የሚጠበቅባቸውን መወጣት እንዲችሉ የተቀናጀ ድጋፍ መደረግ አለበት፤
2. በአውትግሮወር የግብይት ሥርዓት ሊከናወኑ የሚገባቸው ተግባራት እሴት ሰንሰለት መሠረት በማድረግ በዝርዝር እንዲለዩ መደረግ አለበት፤

3. የግብርና ጥሬ ዕቃ አምራቾችና በከፊል እሴት የሚጨምሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የመካከለኛና ከፍተኛ አግሮፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪዎች በሚሰጥዋቸው የምርት ዲዛይን፣ ጥራት፣ ስታንዳርድና መስፈርት መሠረት እንዲያመርቱ የተቀናጀ ድጋፍ መደረግ አለበት፤
4. በክልሉ ውስጥ በአውትግሮውር የግብይት ሥርዓት ሊከናወኑ የሚቻልባቸውን የግብርና ምርቶችን ዝርዝርና የሚገኙባቸውን ቦታዎች ከክልሉና በየደረጃው ካሉ የግብርና ቢሮዎችና የግብርና ምርምር ተቋሞች ጋር የክልሉ ቢሮዎች፣ ኤጀንሲዎች ወይም ጽህፈት ቤቶች የጋራ ዕቅድ በማዘጋጀት ተግባራዊ መደረግ አለበት፤
5. በአውትግሮወር የግብይት ሥርዓት የሚሳተፉ ተዋንያን ሕጋዊ አደራጃጀት፣ የግብይት ውል አፈፃፀም፣ የአቅም ግንባታ ሥራዎች በተመለከተ ዝርዝር አሠራር እንዲኖረው መደረግ አለበት፡፡

18. <u>ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የገበያ ትስስር የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች</u>

ኢንተርፕራይዝ ወይም ኢንዱስትሪ ከገበያ ትስስር ውጭ የሚሆነው፡-

1. የተሰጠውን ስራ በገባው ውል መሰረት መፈጸም ሳይችል ሲቀር፣
2. የተጭበረበረ መረጃ አቅርቦ ሲገኝ፤
3. በዕድገት ደረጃው የተቀመጠለትን የገበያ ትስስር ጣሪያ ሲያልፍ፣
4. ህጋዊ ሰውነት በህግ አግባብ ሲታገድና ሲፈርስ፣

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የኢንተርፕራይዞችን ወይም ኢንዱስትሪዎችን ምርትና አገልግሎት ማስተዋወቅ</u>

19. ስለ<u>ምርትና አገልግሎት የማስተዋወቂያ ስልቶች</u>

1. በኤግዚቢሽንና ባዛር፣
2. በድረ-ገጽ፣
3. በዳይሬክተሪ፣
4. በካታሎግ፣
5. የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራት ሱቆች፣
6. በምርት ማሳያና መሸጫ ሱቅ፣

7. በመጽሔት፣ በብሮሸር፣ በበራሪ ወረቀት እና ቢዝነስ ካርድ፣
8. በቴሌቪዥንና ሬዲዮ፣
9. በቢል-ቦርድ፣
10. በታዋቂ ሰዎች፣
11. የቅዳሜና እሁድ ቀን ገበያ፣
12. በህዝብ መሰብሰቢያ ስፍራዎች፡፡

20. <u>**በኤግዚቢሽንና ባዛር ምርትና አገልግሎት ስለማስተዋወቅ**</u>

1. የኢግዚቢሽንና ባዛር አዘገጃጀትን በተመለከተ የሚከተሉትን ማሟላት አለባቸው፡-
   ሀ) በአዲስ አበባ ከተማ ክልል የሚዘጋጅ የኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ኢግዚቢሽንና ባዛር ደረጃውን የጠበቀ መሆን አለበት፤
   ለ) የኢግዚቢሽን እና ባዛሩን ደረጃ ከፍ ለማድረግ የሚያግዙ መረጃዎችን በማሰባሰብ ለባለሙያዎችና ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የግንዛቤ ፈጠራ ስልጠናዎች መዘጋጀት አለባቸው፤
   ሐ) ኢግዚቢሽንና ባዛር የሚዘጋጅበት ቦታ ብዙ ህዝብ የሚንቀሳቀስበት ቦታ እና ሰፊ ገበያ ዕድል የሚፈጥር መሆን አለበት፤
   መ) ኢግዚቢሽንና ባዛር ሲዘጋጅ የትራፊክ ፍሰትን የማያስተጓጉል እና ለአደጋ ያልተጋለጠ መሆን አለበት፤
2. በኤግዚቢሽንና ባዛር የሚሳተፉ የኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ምልመላን የኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ምልመላ ዕድገት ተኮር ዘርፍ ላይ የተሰማራ ሆኖ፡-
   ሀ) በበጀት ዓመቱ የታደሰ ዕድገት ደረጃ ማቅረብ አለበት፤
   ለ) እድገት ተኮር የስራ ዘርፍ ላይ የተሰማራ መሆን አለበት፤
   ሐ) ከንግድ ዘርፍ ውጪ ያለ ኢንተርፕራይዝ ወይም ኢንዱስትሪ የራሱን ምርት ብቻ ይዞ መግባት አለበት፤
   መ) በኤግዚቢሽንና ባዛሩ ከመጀመሩ በፊት በቂ ምርት ያለው መሆን አለበት፡፡

3. በኤግዚቢሽንና ባዛር ላይ የሚሳተፉ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን በተመለከተ የሚከተሉትን ማሟላት አለባቸው፡-

ሀ) አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የሚጠቀም፤

ለ) የፈጠራ ስራ ያለው፤

ሐ) የውጪ ምርት የሚተካ ምርት የያዘ፤

መ) ሞዴል ኢንተርፕራይዝ ወይም ኢንዱስትሪ የሆነ፤

ሠ) ለበርካታ ዜጎች የስራ ዕድል የፈጠረ፤

ረ) ምርታቸውን ወደ ውጪ ሀገር ለሚልኩ፤

ሰ) አካል ጉዳተኛነትን እና ኤች አይ ቪ ኤድስ በደማቸው ያለ፤

ሸ) ሴቶችና ወጣቶችን፣ ከስደት ተመላሾችን፣ የዩኒቨርሲቲና የቴክኒክን ሙያ ምሩቃን አንቀሳቃሾችን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፤

4. የኤግዚቢሽንና ባዛር ተሳትፎን በተመለከተ

ሀ) በኤግዚቢሽንና ባዛር የሚሳተፉ አምራች ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች 60%፣

ለ) ከተማ ግብርናና አገልግሎት ሰጪ 25% መሆን አለበት፤

ሐ) በንግድ ዘርፍ የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች በኤግዚቢሽንና ባዛር ላይ ተሳታፊ የሚሆኑት 15% መሆን አለበት፤

5. ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች በኤግዚቢሽንና ባዛር ለመሳተፍ የሚከተሉትን ማሟላት አለባቸው፡-

ሀ) ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ከኤግዚቢሽንና ባዛር አዘጋጅ አካል በተሰጣቸው ምርትና አገልግሎት ማስተዋወቂያ ቦታ የኢንተርፕራይዙን ማንነት የሚገልጽ ቢዝነስ ካርድ፣ ባነር ማዘጋጀትና ማስዋብ አለባቸው፤

ለ) በኤግዚቢሽንና ባዛር የተሳተፉ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች አዘጋጁ አካል የሚጠይቃቸውን አጠቃላይ መረጃ መስጠት አለባቸው፤

ሐ) በከተማ አስተዳደር የሚዘጋጁ ኤግዚቢሽንና ባዛር ባለው ክፍት ቦታ ላይ ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸው የሌሎች ክልሎች ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የሚጠቀሙ፣ የፈጠራ ስራ ያላቸው፣ ለበርካታ ዜጎች የስራ ዕድል የፈጠሩ፣ ምርታቸውን ወደ ውጪ ሀገር የሚልኩ እና የውጪ ምርት የሚተኩ መሆን አለባቸው፤

6. ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ከክፍለ ከተማቸው ወይም ከወረዳቸው ውጪ ተሳትፎን የሚያደርጉ የሚከተሉትን ማሟላት አለባቸው፡-

ሀ) አዘጋጁ አካል ያደራጃቸውን ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ቅድሚያ በመስጠት ተጨማሪ ቦታ ካለው ብቻ ከሌላ ክፍለ ከተማ ወይም ወረዳ ማሳተፍ ይችላሉ፤

ለ) ከሌላ ክፍለ ከተማ ወይም ወረዳ መጥተው የሚሳተፉ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የሚጠቀሙ፣ የፈጠራ ስራ ያላቸው፣ ለበርካታ ዜጎች የስራ ዕድል የፈጠሩ፣ ምርታቸውን ወደ ውጪ ሀገር የሚልኩ እና የውጪ ምርት የሚተኩ መሆን አለባቸው፡፡

7. በከተማ ደረጃ ኤግዚቢሽንና ባዛር የሚከተሉትን ማሟላት አለባቸው፡-

ሀ) በከተማ ደረጃ በጀትን መሰረት ያደረገ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የደረሱበትን ደረጃ እና ውጤታማነትን የሚያሳይ ኤግዚቢሽንና ባዛር በዓመት ቢያንስ ሁለት ጊዜ መዘጋጀት አለበት፤

ለ) ከተለያዩ ክልሎች የሚመጡ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ቢሮው በሚያዘጋጀው ኢግዚቢሽንና ባዛር ላይ ባለው ክፍት ቦታ ላይ ሊያሳትፋቸው ይችላል፤

ሐ) በከተማ ደረጃ የሚዘጋጅ ኤግዚቢሽን እና ባዛር በማምረት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ በዋናነት ሞዴል፤ በመብቃት፤መካከለኛና ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ቅድሚያ በመስጠት ሌሎችም እንዲሳተፉ መደረግ አለበት፤

መ) በከተማ ደረጃ የሚዘጋጅ ኤግዚቢሽንና ባዛር እንደ መደበኛ ስራ ተወስዶ የሚከናወን ሲሆን ኢንተርፕራይዞች ሙሉም ሆነ ግማሽ ክፍያ ሊሸፍኑ ይችላሉ፤

ሠ) ኢግዚቢሽንና ባዛር በዓመት አንድ ጊዜ የሚዘጋጅ ሆኖ የአንድ ዙር ዝግጅት የቆይታ ጊዜ ከሰባት ቀን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

8. በክፍለ ከተማ ደረጃ ደረጃ ኤግዚቢሽንና ባዛር ለማዘጋጀት የሚከተሉት መሟላት አለባቸው፡-

ሀ) በክፍለ ከተማ ደረጃ በጀትን መሰረት ያደረገ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የደረሱበትን ደረጃ እና ውጤታማነት የሚያሳይ ኤግዚቢሽንና ባዛር መዘጋጀት አለበት፤

ለ) በክፍለ ከተማ ደረጃ የሚዘጋጅ ኤግዚቢሽን እና ባዛር በዋናነት በሞዴል እና ታዳጊ የዕድገት ደረጃ የሚገኙ በማምረት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ቅድሚያ በመስጠት ሌሎቹንም ዘርፎች እንዲሳተፉ መደረግ አለበት፤

ሐ) በክፍለከተማ በሚዘጋጅ ኤግዚቢሽንና ባዛር ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ሙሉም ሆነ ግማሽ ክፍያ ሊሸፍኑ ይችላሉ፤

መ) ኢግዚቢሽንና ባዛር ቢያንስ በዓመት አራት ጊዜ የሚዘጋጅ ሆኖ የአንድ ዙር ዝግጅት የቆይታ ጊዜ ከሰባት ቀን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

9. በወረዳ ደረጃ ኤግዚቢሽንና ባዛር ለማዘጋጀት የሚከተሉት መሟላት አለባቸው፡-

ሀ) ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የደረሱበትን ደረጃ እና ውጤታማነት የሚያሳይ ኤግዚቢሽንና ባዛር መዘጋጀት አለበት፤

ለ) የሚዘጋጅ ኤግዚቢሽን እና ባዛር በዋናነት በማምረት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ የዕድገት ደረጃቸው ጀማሪ ለሆኑ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ቅድሚያ በመስጠት ሌሎቹንም ዘርፎች የሚያሳትፍ መሆን አለበት፤

ሐ) በሚዘጋጅ ኤግዚቢሽንና ባዛር ሁሉም ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ሙሉም ሆነ ግማሽ ክፍያ ሊሸፍኑ ይችላሉ፤፤

መ) ኢግዚቢሽንና ባዛር በዓመትሁለት ጊዜ የሚዘጋጅ ሆኖ የአንድ ዙር ዝግጅት የቆይታ ጊዜ ከሰባት ቀን ያላነሰ መሆን አለበት፤

ሠ) አንድ ወረዳ ለብቻው ኤግዚቢሽንና ባዛር ማዘጋጀት የማይችል ከሆነ ከሌሎች ወረዳዎች ጋር በመቀናጀት ኤግዚቢሽንና ባዛር ማዘጋጀት ይችላል፡፡

10. በክልሎች ስለሚካሄድ ኤግዚቢሽንና ባዛር የሚከተሉት መሟላት አለባቸው፡-

ሀ) በክልሎች የሚዘጋጅ ኤግዚቢሽንና ባዛር መረጃ በማሰባሰብ እና ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች እንዲሳተፉ ኮታ እንዲያዝላቸው በማድረግ የትብብር ስራ መሰራት አለበት፤

ለ) በክልል ደረጃ ለሚዘጋጅ ኤግዚቢሽንና ባዛር ክልሎች በሚሰጡት ኮታና መስፈርት መሰረት ኢንተርፕራይዞችን ወይም ኢንዱስትሪዎችን በመመልመል የማሳተፍ ስራ መሰራት አለበት፤

11. በውጪ ሀገር ለሚዘጋጁ ኤግዚቢሽንና ባዛር የሚከተሉት መሟላት አለባቸው፡-

ሀ) በውጪ ሀገር የሚዘጋጅ ኤግዚቢሽንና ባዛር መረጃ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች በማሰባሰብ እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በመስራት በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች በኤግዚቪሽንና ባዛር እንዲካፈሉ ከአዘጋጁ አካል ጋር ግንኙነት በመፍጠር አጠቃላይ ወጪ እና የተያያዥ መስፈርቶችን መረጃ ለኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች መስጠት አለበት፤

ሐ) በውጭ ሀገር ደረጃ በሚዘጋጅ ኤግዚቢሽንና ባዛር ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች እንዲሳተፉ የመመልመል ስራ መሰራት አለበት፤

መ) ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች በውጪ ሀገራት በሚዘጋጁ ኤግዚቪሽንና ባዛሮች ላይ ለመሳተፍ ለሚያቀርቡት የድጋፍ ጥያቄ ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት አስፈላጊውን የትብብር ደብዳቤ እንዲፃፍላቸው መደረግ አለበት፡፡

21.<u>ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች በኢግዚቢሽንና ባዛር ላይ እንዳይሳተፉ ስለመከልከል</u>

1. የዕድገት ደረጃ የሌለው ወይም የዕድገት ደረጃውን ያላደሰ፣
2. የውጭ ሀገር ምርቶች ይዞ የተገኘ፣
3. በንግድ ዘርፍ የተደራጁ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች በሀገር ውስጥ ከተመረተ ምርት ውጪ ይዞ ከተገኘ፤
4. አምራች ኢንዱስትሪዎች ከሆኑ በሌሎች ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የተመረቱ ምርቶች ይዘው ከተገኙ፤
5. የተሰጣቸውን የኢግዚቢሽንና ባዛር ቦታ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለሶስተኛ ወገን አሳልፈው ከሰጡ፤
6. በኢግዚቢሽንና ባዛር ላይ የሚሳተፍ ኢንተርፕራይዝ ወይም ኢንዱስትሪ ሰላማዊ እንቅስቃሴ ካወከ፤
7. ኢግዚቢሽንና ባዛሩን የሚመለከት ማንኛውንም መረጃ ለሚመለከተው አካል ካልሰጠ፤
8. ሳይፈቀድለት በኢግቢሽንና ባዛሩ ላይ ተሳታፊ ሆኖ ከተገኘ፤ ከኢግዚብሽንና ባዛር ይከለከላል፡፡

22.<u>ኢግዚቢሽንና ባዛር ክልከላን በሚተላለፍ ኢንተርፕራይዝ ወይም ኢንዱስትሪ ላይ የሚወሰድ እርምጃ</u>

1. የተከለከሉ ተግባራትን ለመጀመሪያ ጊዜ የተላለፈ ኢንተርፕራይዝ ወይም ኢንዱስትሪ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት በኢግዚቢሽንና ባዛሩ ላይ እንዲይሳተፍ መደረግ አለበት፤
2. የተከለከሉ ተግባራትን ለሁለተኛ ጊዜ የተላለፈ ኢንተርፕራይዝ ወይም ኢንዱስትሪ በኢግዚቢሽንና ባዛሩ ላይ ለስድስት ወር እንዳይሳተፍ መደረግ አለበት፤
3. የተከለከሉ ተግባራትን ለሶስተኛ ጊዜ የተላለፈ ኢንተርፕራይዝ ወይም ኢንዱስትሪ በኢግዚቢሽንና ባዛሩ ላይ ለአንድ ዓመት እንዲይሳተፍ መደረግ አለበት፡፡

## 23. <u>በኢምፖሪየም ምርትና አገልግሎትን ማስተዋወቅና መሸጥን በተመለከተ</u>

1. ኢንተርፕራይዞችን ወይም ኢንዱስትሪዎችን በመመለልመል ለተወሰነ ጊዜ በኢምፖሪየም ምርትና አገልግሎታቸውን እንዲያስተዋውቁ እና እንዲሸጡ መደረግ አለበት፤
2. ኢንተርፕራይዞችን ወይም ኢንዱስትሪዎችን ወደ ኢምፖሪየም ከገቡ በኋላ በኢምፖሪየሙ የአስተዳደር ስርዓት መሰረት የሚተዳደሩ መሆን አለበት፤
3. በአምራች ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ከራሳቸው ምርት ውጪ በሌሎች ኢንተርፕራይዞች ወይም ድርጅቶች የተመረቱ ምርቶች ይዘው መግባት የለባቸውም፡፡

## 24. <u>በድረ- ገጽ ስለሚደረግ የማስተዋወቅ ተግባር</u>

1. ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ምርትና አገልግሎቶችን በዘርፍ፤ በምስል፤ በዋጋና በሚገኙበት አድራሻ በዝርዝር በመለየት በቢሮውና በክፍለ ከተማ በሚዘጋጅ ድረ-ገጽ እንዲለቀቅ በማድረግ፤በየጊዜውም መረጃው እንዲስተካከል መደረግ አለበት፤
2. ከኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ምርትና አገልግሎት ለመግዛት ለሚፈልጉ የውጪ፣የሀገር ውስጥ ድርጅቶች እና ግለሰቦች የተሟላ መረጃ በድረ-ገጽ በኩል እንዲያገኙ የማድረግ ስራ መሰራት አለበት፤
3. ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች በኤሌክትሮኒክስ ግብይት ከሚሰሩ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ምርትና አገልግሎታቸውን የማስተዋወቅ እና የመሸጥ ስራ እንዲያከናውኑ ድጋፍ መደረግ አለበት፡፡

## 25. <u>በዳይሬክተሪ የሚደረግ የማስተዋወቅ ስራን በተመለከተ</u>

1. ዳይሬክተሪ በማዘጋጀት የኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ምርትና አገልግሎት የማስተዋወቅ ስራ መሰራት አለበት፤
2. የኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ምርትና አገልግሎት አጠቃላይ መረጃ

   ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት የማሰባሰብ፣ የማሳተም እና በድረ-ገጽ በመልቀቅ የማስተዋወቅ ስራ መሰራት አለበት፡፡

## 26. በካታሎግ ስለሚደረግ የማስተዋወቅ ተግባር

1. ካታሎግ በማዘጋጀት የኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ምርትና አገልግሎት የማስተዋወቅ ስራ መሰራት አለበት፤
2. የኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ምርትና አገልግሎት አጠቃላይ መረጃ በምስል በተደገፈ መልኩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት የማሰባሰብ፣ የማሳተም እና በድረ-ገጽ በመልቀቅ የማስተዋወቅ ስራ መሰራት አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## ለኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የጥሬ ዕቃ/ግብአት አቅርቦት

## 27. የጥሬ እቃ አቅርቦትን ስለማመቻቸት

1. ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች በአካባቢ፣ በክልል እና በውጪ ገበያ በጥሬ ዕቃ አቅርቦት ያሉባቸውን ችግር በመለየት እና ድጋፍ በማድረግ ተወዳዳሪነታቸውን የማሳደግ በቅንጅት የሚገዙበት ስራ መሰራት አለበት፤
2. የኢንተርፕራይዞችን ወይም ኢንዱስትሪዎችን የጥሬ እቃ ፍላጎት ለማመቻቸት እንዲቻል በየክላስተር ማዕከሉ የሚገኙ አምራቾች የጥሬ ዕቃ ፍላጎት በዝርዝር በዓይነት፣ በዋጋ፣በጥሬ ዕቃው መገኛ ቦታ እና በመጓጓዣ ወጪ ተለይቶ መዘጋጀት አለበት፤
3. በኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የጥሬ ዕቃ ፍላጎት መሰረት ከጥሬ ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች ጋር እና አርስ በርስ ግንኙነት በመፍጠር ግዢ ለመፈፀም ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠርላቸው ድጋፍ መደረግ አለበት፤
4. በክላስተር ማዕከላት የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የጥሬ ዕቃ ፍላጎታቸውን መሰረት በማድረግ የጋራ ግዢ እንዲፈጽሙ ድጋፍ መደረግ አለበት፤
5. በጥሬ ዕቃ አቅራቢነት ለተደራጁ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች በክላስተር ማዕከላት ጥሬ ዕቃ እንዲያቀርቡ የማመቻቸት ስራ መሰራት አለበት፤
6. የኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የእርስ በርስ ግንኙነትን በማጠናከር፣ በከተማችን ከሚገኙ ተቋማት እና በክልሎች ከሚገኙ ተቋማት ጋር የምርትና የግብዓት ቅብብሎሽ ማመቻቸት ስራ መሰራት አለበት፡፡

## ክፍል ስድስት

## በየደረጃው የሚገኙ አስፈጻሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 28. የቢሮው ተግባርና ኃላፊነት

የከተማ አስተዳደሩን አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 የተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆኖ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ይረዳ ዘንድ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. የገበያ ልማትና ፕሮሞሽንን በተመለከተ ለዘርፉ ባለሙያዎች፣ ባለድርሻ አካላትና ለኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ግንዛቤ እንዲፈጠር ይደረጋል፤
2. የሀገር ውስጥ ገበያ ጥናት በማድረግ ለኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የምርት ግብዓትነት የሚያገለግሉ እና ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በማጥናት በኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የሚመረቱበትን ሁኔታዎች የማመቻቸት ስራ ይሰራል፤
3. ምርቶቻቸውን ኤክስፖርት ሊያደርጉ የሚችሉ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች በመለየት ምርቶቻቸውን በውጪ ሀገር ካሉ ኩባንያዎች ጋር እንዲተሳሰሩ ያደርጋል፤
4. ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች በኤክስፖርት ንግዱ እንዲገቡ ከሚያግዙ ተቋማት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤
5. የክልል የገበያ ዕድሎችን በማጥናት በክልሉ ካሉ ተመሳሳይ ቢሮዎች ጋር በመነጋገር አምራችና አከፋፋይ ዮኒዮኖች፣ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ከተደራጁ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ጋር ትስስር የሚፈጥሩበትን ሁኔታ የማመቻቸት ስራ ይሰራል፤
6. በአካባቢ የሚገኙ የገበያ ዕድሎችን በጥናት በመለየት ለክፍለ ከተማ እና ለወረዳ ጽህፈት ቤቶች መረጃ ይሰጣል፤
7. ወደ ኢምፖሪየም የሚገቡ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን በመስፈርቱ መሰረት እንዲመለመሉ ያደርጋል፤ ይከታተላል፤ ይደግፋል፤
8. ለኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች በአውትሶርሲንግ፣ በፍራንቻይዚንግ፣ በሰብ ኮንትራክቲንግ፤ በአውትግሮወርና በኮንሳይመንት የገበያ ዕድሎችን እንዲያገኙ የማመቻቸት ስራ ይሰራል፣ ያስተባብራል፤

9. ጥሬ ዕቃ የሚያስፈልጋቸውን ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን በመለየት ከአምራችና ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር የማስተሳሰር ስራ ይሰራል፣ ስራውን በበላይነት ያስተባብራል፤

10. ከተማ አቀፍ ኢግዝቢሽንና ባዛር በማዘጋጀት የኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ምርትና አገልግሎታቸውን ያስተዋውቃል፤

11. በውጭ ሀገር ኢግዚቢሽንና ባዛር ላይ የሚሳተፉ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን ይመለምላል፣ በጀት ይይዛል፤ ያስተባብራል፤

12. በከተማ ደረጃ የተለየ የቅዳሜ እና እሁድ ገበያ ስራን ለክፍለ ከተሞች ይደለድላል፣ ይመራል፤ያስተባብራል፤

13. ድረ-ገጽ፣ ካታሎግ፣ ዳይሬክተሪ፣ መጽሄት፣ ሬዲዮና ቴሌቪዥን እና ሌሎች የማስተዋወቂያ መንገዶችን በመመጠቀም የኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን ምርትና አገልግሎት እንዲያስታዋውቁ ያደርጋል፤

14. ለኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች በተለያዩ ተቋማት የተፈጠረላቸውን የገበያ ትስስር መረጃ አጠናቅሮ ይይዛል፣ መረጃውንም ለክፍለ ከተማና ለወረዳ ጽህፈት ቤቶች በተዋረድ እንዲደርስ ያደርጋል፤

15. የተሰጣቸውን የገበያ ትስስር ድጋፍ በአግባቡ በማይጠቀሙ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤እንዲወሰድ ያስተባብራል፤

16. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግዢ መመሪያ መሰረት ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የተደራጁበትን የግል ማህደር እና የታደሰ የዕድገት ደረጃ በኃላፊው ተረጋግጦ የዋስትና ደብዳቤ የብር መጠን ሳይገለጽ እንዲፃፍላቸው ያስተባብራል፤

17. ከመንግስት ግዙፍ ፕሮጀክቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ለኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የገበያ ትስስር እንዲያገኙ ያስተባብራል፤

18. በከተማ ደረጃ የተገኘ የገበያ ትስስርን ለክፍለ ከተማዎች በመስፈርት መሰረት የገበያ ትስስርን አከፋፍሎ ይሰጣል፤ ያስተባብራል፤

19. ከሸማች ማህበራት፣ ዩኒየኖች፣ የንግድ ምክር ቤቶች እና ከተለያዩ ማህበራት ጋር በቅንጅት በመስራት ለኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የገበያ ትስስር ይፈጥራል፤

20. በገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዙሪያ የተሻለ አፈፃፀም ያላቸውን ሀገራትና ክልሎችን በመለየት ተሞክሮ በመውሰድ የተገኙትን ተሞክሮዎች ቀምሮ የማስፋት ስራ ይሰራል፤ ያስተባብራል፤

21. በገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዙሪያ የተሻለ አፈፃጸም ያላቸውን ወረዳዎችና ክፍለ ከተሞች በመለየት ተሞክሮቻቸውን ቀምሮ ለሌሎች ክፍለ ከተማ እና ወረዳዎች የማስፋት ስራ ይሰራል፤

22. በገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዙሪያ መረጃዎችን እና ሪፖርቶችን አጠናቅሮ ይይዛል፣ ለሥራ ኃላፊዎችና ለባለድርሻ አካላት ያሳውቃል፡፡

## 29. የክፍለ ከተማ ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት

1. የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን መመሪያዎችን ያስፈጽማል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል እንዲሻሻሉ ግብዓት ይሰጣል፤ ያስተባብራል፤
2. የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን በተመለከተ ለዘርፉ ባለሙያዎች፣ ባለድርሻ አካላትና ለኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ግንዛቤ ይፈጥራል ያስተባብራል፤
3. የሀገር ውስጥ የገበያ ጥናት በማድረግ በኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ሊመረቱ የሚችሉ እና ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በማጥናት ሁኔታዎች በማመቻቸት መረጃ አደራጅቶ ይይዛል፤ ለሚመለከተው አካል ያስተላልፍል፤
4. ምርቶቻቸውን ኤክስፖርት ሊያደርጉ የሚችሉ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን ይለያል፣ መረጃቸውን አጠናቅሮ ያስተላልፋል፣ የሚገጥማቸውን ችግሮች በመለየት የተሻለ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ ያስተባብራል፤
5. ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች በኤክስፖርት ንግዱ እንዲገቡ ከሚያግዙ ተቋማት ጋር በቅንጅት ይሰራል፤
6. በአካባቢ የሚገኙ የገበያ ዕድሎችን በጥናት በመለየት ከኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ጋር የማስተሳሰር ስራ ይሰራል፣ ያስተባብራል፤

7. ለኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች በአውትሶርሲንግ፣ በፍራንቻይዚግ፣ በንኡስ ስራ ተቋራጭ፤ በአውትግሮወር እና በኮንሳይመንት የገበያ ዕድሎችን የማመቻቸት ስራ ይሰራል፤ ያስተባብራል፤

8. ወደ ኢምፖሪየም የሚገቡ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን በመስፈርቱ መሰረት እንዲመለመሉ ያደርጋል፤ ይከታተላል፤ ይደግፋል፤

9. ጥሬ ዕቃ የሚያስፈልጋቸውን ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን በመለየት ከአምራችና ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር የማስተሳሰር ስራ ይሰራል፣ ስራውን ያስተባብራል፤

10. በጀት በማስያዝ በክፍለ ከተማ ደረጃ ኤግዝቢሽን ባዛር በማዘጋጀት የኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን ምርትና አገልግሎታቸውን ያስተዋውቃል፣ ያስተባብራል፤

11. የቅዳሜና እሁድ ቀን ገበያን በቢሮው በሚሰጠው ኮታ መሰረት ኢንተርፕራይዞችን ይለያል፣ ያሳትፋል በመከታተል የገበያ ትስስር መረጃን አደራጅቶ ይይዛል፤

12. ድረ-ገጽ፣ ካታሎግ፣ ዳይሬክተሪ፣ መጽሄት እና ሌሎች የማስተዋወቂያ መንገዶችን በመጠቀም የኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን ምርትና አገልግሎት ያስተዋውቃል፤ ያስተባብራል፤

13. ለኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች በተለያዩ ተቋማት የተፈጠረላቸውን የገበያ ትስስር መረጃ አጠናቅሮ ይይዛል፣ መረጃውን በተዋረድ እንዲደርስ ያደርጋል ያስተባብራል፤

14. የተሰጣቸውን የገበያ ትስስር ድጋፍ በአግባቡ በማይጠቀሙ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤ ያስተባብራል፤

15. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስና ግዢ መመሪያ መሰረት ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የተደራጁበትን የግል ማህደር እና የታደሰ የዕድገት ደረጃ በኃላፊው ተረጋግጦ በዘርፉ የሚፈጠረው የመንግስት የገበያ ትስስር ጣሪያ ድረስ ብቻ የዋስትና ደብዳቤ የብር መጠን ሳይገለጽ እንዲፃፍላቸው ያስተባብራል፤

16. በክፍለ ከተማ ደረጃ የተገኘ የገበያ ትስስርን ለወረዳ በመስፈርት መሰረት አከፋፍሎ ይሰጣል፣ ያስተባብራል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

17. ሸማች ማህበራትና ዩኒየኖች የንግድ ምክርቤቶች እና ከተለያዩ ማህበራት ጋር በቅንጅት በመስራት ለኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የገበያ ትስስር ይፈጥራል፣ ያስተባብራል፣

18. በገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዙሪያ መረጃዎችን እና ሪፖርቶችን አጠናቅሮ ይይዛል፣ ለበላይና ለባለድርሻ አካላት ያሳውቃል፡፡

30. <u>የወረዳ ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. በገበያ ልማትና ፕሮሞሽን አሰራር መሰረት የተሰጡትን ተግባራት ይፈፅማል፣
2. ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን በአካባቢው ከሚገኙ መካከለኛ ወይም ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በተለያየ አግባብ የሚተሳሰሩበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ሁለቱንም አካላት የሚፈልጉትን መለየት፣ የማወያየትና ትስስር የሚፈጠርበትን ስልት ይቀይሳል፣ ያስተባብራል፣
3. ኢንተርፕራይዞች በአካባቢው ከሚገኙ የመንግስት፣ የግልና ሌሎች ድርጅቶች ጋር በንዑስ ተቋራጭነት፣ በአውትሶርሲንግ፣ በፍራንቻይዚንግ፣ በአውትግሮወር እና በኮንሳይመንት የትስስር ሥርዓቶች ተሳስረው የሚሰሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ያስተባብራል፣
4. በአካባቢው የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን ምርትና አገልግሎቶች ፕሮፋይል በማዘጋጀት ስራ ሊሰጡ ወይም ምርትና አገልግሎት ሊወስዱ ለሚችሉ ድርጅቶች በልዩ ልዩ ዘዴ ያስተዋውቃል፣ ያስተባብራል፣
5. በኢንዱስትሪ ማዕከላት በመገኘት ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን የሚያስፈልጋቸውን የጥሬ ዕቃ አይነት በመጠን በዋጋና በጥራት ደረጃ በዝርዝር በመለየት ጥሬ ዕቃው የሚገኝበትንና በጅምላ ግዢ እንዲፈጽሙ ምክርና ድጋፍ እንዲሰጣቸው ያደርጋል፣ ያስተባብራል፣
6. በወረዳ ደረጃ በሚዘጋጁ ኤግዚቢሽንና ባዛሮች በእቅዱ መሰርት በጀት በመያዝ ወቅቱን ጠብቆ እንዲፈፀም ያደርጋል፣
7. በወረዳ ደረጃ ራሱን ችሎ ኢግዚቢሽንና ባዛር ማዘጋጀት ካልቻለ ከአጎራባች ወረዳዎች ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፣ ያስተባብራል፣

8. የቅዳሜና እሁድ ቀን ገበያን ክፍለ ከተማ በሚሰጠው ኮታ መሰረት ኢንተርፕራይዞችን ይመለምላል፣ መረጃ በማደራጀትም ለክፍለ ከተማ ያስተላልፋል፣ የሚሳተፉትንም በመከታተል የገበያ ትስስር መረጃን አደራጅቶ ይይዛል፡፡

9. ወደ ኢምፖሪየም የሚገቡ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን በመስፈርቱ መሰረት ይመለምላል፤ ይከታተላል፤ ይደግፋል፤

10. በገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ሂደት የተሻለ እንቅስቃሴ ያደረጉና ሞዴል የሚሆኑ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች በመለየት ተሞክሮ እንዲሰፋ ያደርጋል፤ ያስተባብራል፤

11. የገበያ ትስስር የተደረገላቸው ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ሙሉ መረጃ በተደራጀመንገድ እንዲያዝ ያደርጋል፤

12. ከተለያዩ ተቋማት ጋር በሚደረገው የገበያ ትስስር በኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች የሚሰሩ ስራዎችን በመለየት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ድጋፍ ያደርጋል፤

13. ምርቶቻቸውን ኤክስፖርት ሊያደርጉ የሚችሉ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን የመለየት ስራ በመስራት ለሚመለከታቸው አካላት መረጃውን ያስተላልፋል፤

14. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፋይናንስና ግዢ መመሪያ መሰረት በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የተደራጁበትን የግል ማህደር እና የታደሰ የዕድገት ደረጃ በኃላፊው ተረጋግጦ በዘርፉ የሚፈጠረው የመንግስት የገበያ ትስስር ጣሪያ ድረስ ብቻ የዋስትና ደብዳቤ የብር መጠን ሳይገለጽ እንዲፃፍላቸው ያደርጋል፤

15. በገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዙሪያ መረጃዎችን እና ሪፖርቶችን አጠናቅሮ ይይዛል፣ ለሥራ መሪዎችና ለባለድርሻ አካላት ያሳውቃል፡፡

## ክፍል ሰባት

## መብቶችና ግዴታዎች

### 31. የገበያ ድጋፍ ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች መብት

1. ወቅታዊ የገበያ መረጃ ማግኘት፤
2. የንግድ ስራ አመራር ስልጠና ድጋፍ ማግኘት፤
3. ምርትና አገልግሎቱን በአካባቢ ገበያ ለማስተዋወቅ በየደረጃው በሚዘጋጁ ኤግዚቢሽንና ባዛር ላይ የመሳተፍ እንዲሁም በሌሎች የማስተዋወቂያ ዘዴዎች ምርትና አገልግሎትን ማስተዋወቅ፤
4. ፍትሃዊ የገበያ ትስስር ድጋፍ ማግኘት፤
5. በገበያ ትስስር ሂደት በሚፈጠሩ ችግሮች ምክንያት ቅሬታ እና አቤቱታ የማቅረብና መልስ ማግኘት፡፡

### 32. የገበያ ድጋፍ ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ግዴታዎች

1. መንግስት በሚያደርገው ድጋፍ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስፈልጉ ወቅታዊና ህጋዊ ማስረጃዎችን ማቅረብ፤
2. በውሉ መሰረት ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ ምርትና አገልግሎት ማቅረብ፤
3. የተገኘውን የገበያ ዕድል መረጃ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ፤
4. በጨረታ ሲሳተፉ የጨረታውን ሂደት ለማደናቀፍ በማሰብ የተጋነነ ወይም ከገበያ በታች የሆነ ዋጋ ያለማቅረብ፡፡

### 33. በየደረጃው ያለ የፈጻሚ አካላት መብቶች

1. ከኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ከስራ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃ ማግኘት፤
2. ድጋፍ ለማግኘት የቀረቡ መረጃዎች ወቅታዊና ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥ፤
3. ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች መንግስታዊና አስተዳደራዊ ግዴታዎችን እንዲወጡ መከታተል፤
4. የገበያ ዕድል ከሚፈጥሩ ተቋማት አጠቃላይ መረጃ ማግኘት፡፡

34. <u>በየደረጃው ያለ የፈጻሚ አካላት ግዴታ</u>

1. አግባብነት የሌለውና በአሰራር ወይም በዚህ አሰራር ያልተካተተ ድጋፍ ማድረግ የለበትም፤
2. የገበያ ልማት እና ፕሮሞሽን ሥርዓት መመሪያ በአግባቡ ማስፈጸም አለበት፤
3. ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን በገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዙሪያ የመደገፍ፤ የመከታተልና የማብቃት፤
4. ፍትሃዊ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አገልግሎት መስጠት አለበት፤
5. ብልሹ የሆኑ አሰራር መታገል፣ መጠቆም እና በአጥፊዎች ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ አለበት፤
6. የገበያ ድጋፍ የተደረገላቸውን ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን መረጃ በተደራጀ መንገድ መያዝ አለበት፤
7. የገበያ መረጃን ለሁሉም ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎችን እኩል እንዲደርስ ማድረግ አለበት፤
8. የሁሉንም ኢንተርፕራይዞች ወይም ኢንዱስትሪዎች ፕሮፋይል አደራጅቶ መያዝና የገበያ ትስስር ለሚፈጥሩ ተቋማትም በተጠየቀ ጊዜ መስጠት አለበት፤
9. ማንኛውም ኢንተርፕራይዝ ወይም ኢንዱስትሪ ሕጋዊ መሆኑን አጣርቶ የገበያ ትስስር እንዲያገኝ መደረግ አለበት፡፡

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 35. ስለተጠያቂነት

የዚህን መመሪያ ድንጋጌ ጥሶ የተገኘ ማንኛውም ሰው አግባብነት ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 36. የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች

1. የገበያ ልማትና ግብይት ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 74/2014 ተሽሮ በዚህ መመሪያ ተተክቷል፤
2. ይህን መመሪያ የሚቃረኑ ቢሮው ያወጣቸው ማንኛውም መመሪያዎች እና ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ መመሪያ ላይ በተመለከቱት ጉዳዩች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

### 37. መመሪያውን ስለማሻሻል

ቢሮው እንደ አስፈላጊነቱ ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

### 38. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከዛሬ መጋቢት 15 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት 15 ቀን 2014 ዓ.ም**

**ጃንጥራር ዓባይ ይግዛው**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ም/ከንቲባ እና**

**የስራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ**